

## 32-1

# ከአሉባልታ ወሬ እንሽሽ

**ምላስ ከሰይፍ የበለጠ ይጎዳል**

አንድ ጊዜ ውሻው በጣም ያስቸገረችው አንድ ሰው "ከእኔ ጋር ብዙ ጊዜ ቆይተሻል። ስለሆነም ምንም ያህል ብታናድጂኝና ብታበሳጭኝም እኔ አልገድልሽም። ግን መጥፎ ስም እሰጥሻለሁ" አላት። ሕዝብ በብዛት ወደሚገኝበት አደባባይ ወሰዳትና "ሂጂ!" ብሎ ፈትቶ ለቀቃት። ልክ እንደለቀቃት፣ "ዕብድ ውሻ! መርዘኛ ውሻ" ሲል ደጋግሞ ጮኸ። በአደባባዩ የነበረው ሕዝብ ተተረማመሰ የሚችለው እየሮጠ ሸሸ። በመጨረሻ ከሕዝቡ መካከል አንዱ ሽጉጡን አውጥቶ ተኩሶ ገደላት። ከዚያ ሕዝብ መካከል "እስቲ ጊዜ ወስደን ውሻዋ መርዘኛን መሆኗን እናጣራ" ያለ አንድም ሰው አልነበረም። ሁኔታው ጊዜ የማይሰጥ ስለሆነ በመሠረቱ የወሰዱት እርምጃ ትክክል ነበር።

ዛሬ ልክ እንደዚያች ንጹህ ውሻ "በአሉባልታ ሽጉጥ" እየተመቱ የሚቆስሉ የሚባረሩ አገልግሎታቸውን የሚያጡ ከክርስቲያን አንድነትና ሕብረት እንዲሸሹ የሚደረጉ እንዲሁም የሚሞቱ (በመፈሳዊ ሕይወታቸው) ስንቶች ይሆን? ብዛታቸውን ቤታቸው ይቁጠራቸው። በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ በክርስቲያኖች መካከል "የአሉባልታ ሽጉጥ" ሲተኮስ ይሰማል። አደገኛነቱንም የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። "ያለ ጥንቃቄ የተነገረ ቃል እንደ ሰይፍ ያቆስላል" (ምሳሌ 12፥18) ይላል። ይሁን እንጂ ይህ ሰይፍ በብዙዎች ላይ እንዳይመዘዝ የተደረገ ጥንቃቄ የለም።

አንዳንድ ተንኮለኞች ልዩ ድብቅ ዓላማ ኖሯቸው የሚፈልጉትን ሰው ለመግደል ሲሉ "ዕብድ ውሻ! መርዘኛ ውሻ" እያሉ ሌሎችን ለመጉዳት ይጮሃሉ። "ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን ያስባሉ፤ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው። ክፉ ሰዎች ሐሜትን ያሰራጫሉ፣ ሁከትንም በማነሣሣት በፍቅር የተሣሠሩትን ወዳጆች ይለያያሉ" ይላል ምሳሌ 16፥27-28። የአሉባልታው ፈጣሪዎች ከሚጮኹት ይበልጥ የሚያሳዝኑት፥ ምክንያቱን ሳይውቁ እውነትነቱን ሳይረጋግጡ መልሰው "ዕብድ ውሻ መርዘኛ ውሻ" እያሉ የሚያስተጋቡት የዋህ ሰዎች ናቸው። እነዚያ ተንኮለኞች መርዛቸውን አንድ ጊዜ ከረጩ በኋላ የተቀረውን የማስፋፋት ሥራውን የሚሠሩላቸው ምኑንም የማይወቁ አንዳንድ የዋህ ሰዎች ናቸው። "ሐሜትን የሚያሰረጭ ሰው ሞኝ ነው" ይላል ምሳሌ 10፥18።

በክርስቲያኖች መካከል "ለአንድ ሳምንት ያህል የአሉባልታ ወሬ ሀሜት እንዳይኖር" ተብሎ ቢታወጅብን ምን እንሆን ነበር? በአካባቢያችን ፍጹም ጸጥታ ይሰፍን ነበር። ምክንያቱም ከንግግራችንና ከውይይታችን ውስጥ 80% (ሰማንያ ከመቶ) የምናወራው ስለ ሌላው ሰው ስለ ሆነ ነው። እስቲ ይህን ለማረጋገጥ ከዚህ በኋላ ልብ ብለን እንመልከት። የአሉባልታ ወሬ የማውራት ግፊት (compulsive gossip) ያለብን ሌላ የምናወራበት መንገድ ብናጣ "ለእከሌ እንጸልይለት በኃጢአት ወድቋል (ኃጢአቱን አልነግራችሁም) ለወንድማችን እንጸልይለት መንፈስ ቅዱስን ከዱል ይባላል" እንላለን። በዚህ ዘዴ ያስጨነቀንን ለመተንፈስ እንሞክራለን።

በ1920 ዓመት ምሕረት በጀርመን አገር አንድ ክርስቲያኖች በኅብረት የሚኖሩበት የክርስቲያኖች መንደር (ህብረት) ነበር። ኅብረታቸውን ለማጠናከር አንድ ደንብ አውጥተው ነበር። ይኸውም "አንዱ በሌላው ወንድም ሆነ እህት ላይ የሀሜት ቃል የአሉባልታ ወሬ ማሰማት ክልክል ነው" የሚል ሕግ ነበር። ክርስቶስም በተራራው ስብከቱ ላይ ለተከታዮቹ ያስተላልፍ ከነበረው ትምህርት አንደኛው ይሄ ነበር። "በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ዓይነት በእናንተም ላይ ይፍረድባችኋል እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል" ይላል ማቴዎስ 7፥1-5። ታዲያ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እየተናገረ "የአሉባልታ ጥይት" በወገኖቻችን ላይ እኔና እናንተ የምንተኩሰው ለምን ይሆን? የአሉባልታን አደገኛነት ለመግለጽ የሞከረው ብሌዝ ፓስካል "ሰው ሁሉ አንዱ ስለ ሌላው ምን እንደሚል የማወቅ ኃይል ቢኖረው ኖሮ በዓለም ውስጥ ከአራት የሚበልጡ ጓደኛሞች እንደማይኖሩ እርግጠኛ ነኝ" አለ። አሉባልታ የሚዋደዱትን ጓደኞች እንደሚለያይ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል (ምሳሌ 20፥19)።

## አሉባልታ ምንድነው?

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ "አሉባልታ ሆን ብሎ የሌላውን ሰው ስም የሚያጎድፍ የሞግዳ ሪፖርት መስጠት ነው።" የተነገረው ወሬ እውነትም ይሁን ውሸት ስለ ሌላው መጥፎ ሪፖርት የሚሰጥ ከሆነ "አሉባልታ" ነው። አሉባልታ የክርስቲያኖችን ኅብረት ቀስ በቀስ በልቶ የሚጨርስ ነቀርሳ ነው። አሉባልታ የተቀራረቡትን የሚለያይ፣ የሚዋደዱትን የሚያጋጭ መርዝ ነው። አሉባልታ የሰለጠነበት አሉባልታ እንዲያድግ ዕድል ያገኘበት ኅብረተሰብ ብዙ ዕድሜ ሳይኖረው ቶሎ ይፈርሳል። ስለሆነም፥ በኅብረታችን ውስጥ ይሄ የአንድነት ነቀርሳ የሆነው "አሉባልታ" ዕድል እንዳያገኝ መጠንቀቅ ይገባናል።

## አሉባልታ ጎጂ ነው

ያዕቆብ ያለቦታው ያልዋለ ምላስ ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ገልጾአል። "ምላስ እንደ እሳት ናት፤ ምላስ በአካል ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፤ ሥጋችንንም ሁሉ ታረክሳለች፤ እንደ ገሃነም እሳት ሰውነታችንን ሁሉ ታቃጥላለች" ይላል ያዕቆብ 3፥6። ሺለር የተባለው ሰው "በዓለም ላይ በመርዝና በሰይፍ ከሞቱት ይልቅ በሰላዮችና በአሉባልታ አውሬዎች ምክንያት የሞቱት ይበልጣሉ" አለ። አሉባልታ ከመጠን በላይ ጎጂ ነው። በአሉባልታ ምክንያት ብዙዎች ሰው እንዳይቀርባቸው ሰው እንዲሸሻቸው በማድረግ አገልግሎታቸው ወደ ኋላ እንዲ ትተት ወይንም ያለአግባብ ተፈርዶባቸው ከነጭራሹ ከአገልግሎታቸው የተባረሩ አሉ። በአሉባ ልታ ምክንያት የብዙዎች ስምና ዝና ይጠፋል። ብዙዎች ከሥራቸው ይሰናከላሉ። አሉባልታ በባልና ሚስት መካከል መቃቃር ሲበዛም መፋታትን ያመጣል።

## የአሉባልታ (የሃሜት) ምክንያት ምን ይሆን?

ሰዎች የአሉባልታ የሃሜት ወሬ የሚያሰሙበት ምክንያት ምን ይሆን? ምክንያቶቹ እንደ ሰውየው እንደ ጊዜውና እንደ አካባቢው ይለያያል። ከምክንያቶቹ ጥቂቶችን ከዚህ ቀጥሎ ለማቅረብ ሞክረናል።

1) በልምድ

አንዳንድ ሰው ሳያውቀው መጥፎ ልማድ ውስጥ ይገባል። ሌላውን ሰው ለመጉዳት አስቦ ሳይሆን ስለ ሌላው ሰው ድካም ማውራት ደስ የሚለው ሰው አለ። ስለ ሰው አንስቶ ካወራ 5% (ከመቶ አምስት) ብቻ ብርታቱን ወይንም ጥሩነቱን ሲናገር፥ (95%) (ዘጠና አምስት ከመቶው) ግን ስለ ድካሙና ስለ ውድቀቱ ያወራል። አሉባልታ በማውራት ደስታን የሚያገኙ አሉ። አንዳንድ ሰዎች ሰውን የሚገነባና የሚያሳድግ ነገር መነጋገር ይህን ያህል ስሜታቸውን ሞቅ የሚያደርገው አርዕስት አይሆንላቸውም። ጣዕም ያጡበታል፤ ይደርቅባቸዋል። ባንክሮፍት የተባለ ሰው “የጎረቤቶቻቸውን ሥጋ በሀሜት እየዘለዘሉ መብላት የለመዱ ሰዎች እውነትን መስማት ይህን ያህል አይጥማቸውም” አለ። በአሉባልታና በሃሜት ምክንያት የሚቀራረቡ ወደጅነት የሚፈጥሩ ሰዎች አሉ። በተገናኙ ቁጥር የሚያወሩት ስለሌላው ሰው ኃጢአትና ድክመት ስለሆነ ፍላጎታቸው ይመሳሰላልና እርስ በርሳቸው ይነፋፈቃሉ። አሉባልታ ከሚጠላ ሰው ጋር ግን ብዙ ጊዜ አብሮ ማሳለፍ ደስ አይላቸውም።

2) ሥራ በማጣት

አንዳንዶቻችን ብዙ ሰፊ ጊዜ ስለሚኖረን ያለንን ትርፍ ጊዜ በአግባቡ መጠቀም አናውቅበትም። እርስ በርሳችን ስንገናኝም የምንነጋገርበት አርዕስት እናጣለን። ልምምዳችን የተወሰነ ስለሆነ ስለ ልምምዳችን አናወራም። ስለ አነበብነው መጽሐፍ እንዳንወያይ የመጽሐፍ ማንበብ ልምድ የለንም። ጊዜ አግኝተን የሰማነው ነገር ቢኖር ያለፈው ዕሁድ ስብከት ብቻ ነው። ያም ቢሆን ስለ ስብከቱ ገንቢ የሆነ አስተያየት ከመስጠት ይልቅ ሰባኪውን መዘነጣጠል እንጀምራለን። ሸርዲን የተባለ ሰው ስለዚህ ችግር ሲናገር “በአሉባልታ ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ምን እያደረጋችሁ ነው? ተብለው ቢጠየቁ የሚሰጡት መልስ ውሸት እያናፈስን ነው የሚል ይሆናል። አሉባልታ የሚያወሩ ሰዎች የሚሠሩት ሌላ ሥር ስለሌላቸው ጊዜ ለመግደል ብቻ ሲሉ የሰውን መልካም ስም መልካም ዝና ገድለው ሥጋውን ቆራርጠው እየበሉ እንደሆነ አይታወቃቸውም” አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ፈት ሆነው ከአንዱ ቤት አንዱ ቤት እየዞሩ ነገር ስለሚያመላልሱ መበለቶች ይናገራል። “ከዚህም በላይ ሥራ መፍታትንና በየሰው ቤት መዞርን ይማራሉ፤ ሥራ መፍታት ብቻ ሳይሆን ሰውን የሚያሙ በሰው ነገር የሚገቡና መናገር የማይገባቸውን የሚናገሩ ይሆናሉ” ይላል 1ኛ ጢሞ 5፥13።

3) በምቀኝነት ምክንያት

ዳዊት ጎልያድን በወንጭፍ ወርውሮ ከጣለው በኋላ ንጉሥ ሳኦል ዳዊትን ወደደው ጋሻ ጃግሬውም እንዲሆን አደረገው። ጊዜያዊ ይሁን እንጂ፥ በዳዊትና በንጉሥ ሳኦል መካከል እውነተኛ ፍቅር ነበር። ይሁን እንጂ ቀስ በቀስ ዳዊት የሠራው ጀብዱ እየታወቀና በሰዎች ዘንድ እየተደነቀ ሲመጣ ንጉሥ ሳኦል ትልቅ ቅናት በውስጡ እየሰረጎደ ገባ። ሳኦል የዳዊት ዝና እየገነነና በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ እየሆነ ሲመጣ እያየ መታገስ አልቻለም። ቅናትም ውስጡን እንደ ነቀርሳ እየበላው መጣ። በመጨረሻው ዳዊትን ከአጠገቡ ማባረር እርሱ ባለበት አካባቢ እንዳይገኝ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሊገድለውም ብዙ ሙከራ አደረገ። የዳዊት ሕይወት በእግዚአብሔር እጅ ስለነበረ ብቻ ሊጎዳው አልቻለም። በቅንአት ምክንያት ሌላውን ለመጉዳት ብዙ የአሉባልታ ወሬ የሚረጩ ሰዎች አሉ። የሚቀኑበት ሰው የሚጎዳበትን መንገድ ቀይሰው ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አይመለሱም። ሌላውን ለመጉዳት ወይም ለመግደል የሚያስፈልገው በዓይን የሚታይ ጦር ብቻ ሳይሆን በዓይን የማይታዩ ልዩ ልዩ ድብቅ መሣሪያዎችንም መጠቀም ይቻላል። ከነዚህ

መካከል አንደኛው በሚጠሉት ሰው ላይ የአሉባልታ ወሬ ማስወራት ነው። መጥፎ ወሬ ስለ ሌላው በማውራት ስሙን በማጉደፍ ሰዎች ስለ እርሱ እንዲጠራጠሩ እንዲፈሩት እንዲሸሹት ለማድረግ የሀሰትን ወሬ መርጨት ያንን ሰው በሰይፍ ከመውጋት ይበልጣል።

……………………………………………………………………

**በሚቀጥለው ክፍል እንክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**